# ADDA BILISUMMAA OROMOO

**OROMO LIBERATION FRONT**      **جبهة تحرير اورومو**

Gaafa: 09– 06 - 2014 تاريخ
Date:

Lakk.: 005/stm-abo/2014 رقم
No.:

## ፍንፍኔ ማዕከላዊ የኦሮሚያ ወሳኝ አካል ናት

ኢትዮጵያን በሃይል ጨፍልቆ እየገዛ ያለው የወያኔ-ኢህአዴግ መንግስት የኦሮሞ ህዝብ በትግሉ የተጎናጸፋቸውን መብቶች መቀልበስ ቀጥሎበታል። የሚገርመው ደግሞ ይህ መንግስት በራሱ ጠበብቶች ባረቀቀውና ራሱ ባጸደቀው የኣገሪቷ ህገ-መንግስት የተካተቱ መብቶችን በቀጣይነት እየጣሰ ይገኛል። የፊንፊኔ ከተማ ማስተር ፕላን በሚል በቅርቡ ስልጣን ላይ ባለው መንግስት የተነደፈው እኩይ ካርታ ላለፉት ሁለት ኣስርተ-ዓመታት የኦሮሚያን ድንበር ሲቀራርስ የቆየው የወያኔ መንግስት ድርጊት ኣካል መሆኑን እንገነዘባለን። የኦሮሞን ህዝብ ከመሬቱ የማፈናቀልና ለችግር መዳረግ የወያኔ መንግስት ቋሚ ፖሊሲ ሲሆን ኦሮሞን ማፈናቀል በ1991 ዓ.ም ከተጀመረበት ጊዜ ኣንስቶ እስካሁን ኣልቆመም።

ኣሁን ኣዲስ የተዘጋጀው የፊንፊኔ ከተማ ካርታ ለፊንፊኔ ቅርብ የሆኑትን የኦሮሚያ ከተሞች የሚጠቀልልና የኦሮሚያን ድንበር የሚጋፋ መሆኑን ባለስልጣናቱ ዓይናቸውን ጨፍነው መካድና ኣደንቋሪ ፕሮፓጋንዳቸውን መንዛት የተያያዙት ቢሆንም እነዚህ ልዩ የኦሮሚያ ዞን ከተሞች በተጨባጭ ፊንፊኔ መስተዳድር ስር እየገቡ ናቸው። ይህ ክልሎችን በልማት ማስተሳሰር በሚል ለእኩይ ኣላማ የተነደፈው ካርታ በፊንፊኔ ዙሪያ የሚገኙ የኦሮሚያ መሬቶችንና እንደ ኣቃቂ፣ ዱኩም፣ ሰበታ፣ ቡራዩ፣ ሱሉልታ፣ ለገ-ጣፎ-ለገ-ዳዲና ሰንዳፋ የመሳሰሉ ከተሞችን በፊንፊኔ መስተዳድር ስር ለማስገባት የታቀደ ነው። እነዚህ ስፍራዎችና ከተሞች እስከ 50 ኪሜ ወይ ከዚያ በላይ ከፍንፍኔ ርቀው የሚገኙ ናቸው። ይህ ውሳኔ ያለኦሮሞ ህዝብ ኣዎንታ በወያኔ-ኢህኣዴግ በዘፈቀደ የተደረሰበት ውሳኔ ነው። ሌላው ቀርቶ ለይስሙላም ቢሆን ኦሮሚያን እያስተዳደርኩ ነው የሚለው የወያኔ ተለጣፊ ድርጅት ኦህዴድ እንኳ ይህንን ጉዳይ ውስጠ-ምስጢሩን ኣያውቅም። ፊንፊኔን በሚመለከት የወያኔ የረዥም ጊዜ እቅድ በደቡብ ምስራቅ እስከ ኣዳማና ከዚያም ባሻገር በደቡብ-ምዕራብ እስከ ወሊሶ ወይም ከዚያ በላይ በሰሜን ምስራቅ እስከ ኣማራ ክልል ድንበር ድረስ ሲሆን በምዕራብ እስከ ኣምቦ በመዝለቅ ታላቋን ኣዲስ ኣበባ(ፍንፍኔ) መገንባት ነው። የወያኔ መንግስት የኦሮሞ ህዝብን ከመሬቱ ኣፈናቅሎ ፍንፍኔን(ኣዲስ ኣበባን) ለማስፋፋት የያዘው እቅድ ወሰን የለውም። የት እንደሚቆም ኣይታወቅም፡ መቆሚያም የለውም። እንደዚህ ዓይነቱ እርምጃ የወያኔን የፖለቲካና የኢክኖሚ ጥቅም ብቻ ለማስጠበቅ የሚወሰድ እርምጃ ነው። የኦሮሞን ህዝብ ከመሬቱ የማፈናቀል ተግባር የኦሮሚያን ህልውና ኣደጋ ላይ የሚጥል ከመሆኑም በላይ በሰብዓዊ ፍጡር ላይ የሚፈጸም ወንጀል ነው።

በወያኔ መንግስት በኦሮሞ ህዝብ ላይ እየተፈጸመ ያለው የመሬት ቅምያ ከሱ በፊት የነበሩ የኢትዮጵያ ገዢዎች ሲያራምዱት የነበረው ፖሊሲ ቅጥያ ነው። ከታሪክ እንደምንረዳው የምኒሊክን ወረራ ተከትሎ የተወረረው የኦሮሚያ ምድር የመንዝ የኣማራ ገዢ መደብ የግል ንብረት ነው የሆነው። የምኒሊክን ወረራ ልዩ ከሚያደርግ ኣንዱ የኦሮሞን መሬት ለመኩዋንንቶችና ለወታደሮቹ (ለነፍጠኞች) ኣከፋፍሎ በኦሮሚያ ምድር ላይ እንዲሰፍሩ ማድረጉ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ኣብዛኛው የኦሮሞ መሬት በመንግስት ይዞታ ስር ገብቶ ለሽያጭ ቀረበ። ንጉሠ ነገሥቱ በኦሮሞ መሬት ላይ የበላይነት መብት እንዳለው ታወጀ። በሌላ በኩል ደግሞ ሰሙነኛ በሚል ሰፊ የኦሮሞ መሬት ለኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ቄሶችና ዲያቆናት ተሰጠ። በጊዜው ቄሶቹና ዲያቆናቱ የምኒሊክን ወረራ ለማስፈጸምና የቅኛ ኣገዛዙን ስርዓት ተግባራዊ በማድረጉ ረገድ ትልቅ ሚና ተጫውተዋል። ባጠቃላይ የኦሮሚያ መሬት በሃይል ኦሮሚያ ውስጥ ለሰፈሩ የኣማራ ገዢ መደብ ኣባላት ከፍተኛ

የግቢ ምንጭ ሆነ። የአማራ ገዢ መደብ የተለያዩ በከፍተኛ በብዝበዛ ላይ የተመሰረቱ የመሬት ይዞታ ስርዓቶችን በማምጣት በእርሻና ከብት ርቢ ላይ የተመሰረተውን የኦሮሞን የጋራ ህይወት ኣበላሹት። ከዚህ የተነሳ የኦሮሚያ ማህበራዊ መዋቅሮችና የአሰፋፈር ዘይቤው ተበጠጥሰው እንድጠፉ ተደረጉ። የኦሮሞን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተቋማት ሆነ ብለው ኣወደሟቸው። በኦሮሞ ህዝብ ላይ የተጫነ የአማራ ገዢዎች የመሬትይዞታ የተለያዩ መልኮች ነበረው። እነርሱም በመንግስት ይዞታ ስር የገቡ መሬቶች፤ ለወታደሮች የሚከፋፈል የሻለቃ መሬት፤ ስርዓቱን በታማኝነት ለሚያገለግሉ አስተዳዳሪዎች የሚሰጥ የማደሪያ መሬት፤ ለገዢዎች የሚታረስ ሁዳድ የሚባል መሬት፤ ለቄሶችና ለዲያቆናት የሚሰጥ ሰሙነኛ መሬትና ሌሎችም ነበሩ። በነዚህ ይዞታዎች ላይ የሚኖሩ ኦሮሞዎች ከነመሬቶቹ ለነፍጠኞች ወይ የገዢ መደብ ኣባላት ተከፋፈሉ። በቀዬያቸው ገባር ሆኑ።

ኦሮሚያ በቅኝ ከመያዟ በፊት የመሬት እደላና አስተድደሩ የሚከናወነው በዲሞክራሲያዊ መንገድ በሚመረጡ የገዳ ስርዓት መሪዎች ነበር። በኦሮሞ ባህልና ታሪክ መሬት የጋራ ነው። የገዳ ስርዓት ጠቅላላ ጉባኤ ህግን ለማውጣትም ሆነ ለማሻሻል ስልጣን ነበረው። ከምኒሊክ ወረራ በኋላ ግን የአማራ ሰፋሪ ቅኝ ገዥዎች ወደ ኦሮሚያ መጉርፍ ጋር ተያይዞ ለጥቂት ነፍጠኞች ጥቅም ሲባል የኦሮሞ ህዝብ ከኣያት ቅድመ ኣያቶቹ የወረሰውን መሬቱን ተቀማ። በኦሮሞ ህዝብ አመለካከትና እምነት ሃብት-ንብረት ባለቤትነቱ ላፈራው ነው፤ መሬት ቀደም ሲል የሰፈሩበት ሰዎች ንብረት ነው፤ የማዕድን ውሃ ምንጭ መጀመሪያ ላገኙት ሰዎች ይገባል የሚሉና የመሳሰሉት ናቸው።

ፍንፍኔና አካባቢዋ በታሪክም በህግም ባለቤትነቱ የኦሮሞ ህዝብ ነው። ከምኒሊክ ወረራ በፊት ዛሬ የፍንፍኔ ከተማ የቆመበት ስፍራና አካባቢው ከኦሮሞ ጎሳዎች ኣንዱ የሆነው የቱለማ ቅርንጫፍ የኢኮኖሚና ሃይማኖታዊ ማዕከል ነበር። የፍንፍኔ ከተማ የተመሰረተበት ሰፊ ቦታ የጉለሌ፤ የኤካና ገላን የኦሮሞ ማህበረሰብ ይዞታዎች ነበሩ። ወራሪውን የምኒሊክ ጦር የመራው ደጃዝማች መሸሻ ሰይፉ ፍንፍኔና አካባቢዋን በሃይል ተቆጣጠረው። በኣያት-ቅድመ ኣያቶቻቸው መሬት ላይ ለዘመናት የኖሩ የኦሮሞ ጎሳዎች ከመሬታቸው በሃይል ተፈናቀሉ። ማሳ ላይ የነበሩ የእርሻ ሰብሎችና መንደሮቻቸው በእሳት እንዲጋዩ ተደረገ። የእርሻና ግጦሽ መሬታቸውን ተነጠቁ። በሃይል የተያዙ የኦሮሞ መሬቶች ለመንዝ ልዑላን ቤተሰብ ለነኣጼ ምኒሊክ ቤተሰብ፤ ለነደጃዝማች መሸሻ ሰይፉና ራስ ብሩ ለመሳሰሉ ወራሪዎች ተከፋፈለ። ቀደም ሲል ፍንፍኔ በመባል ይታወቅ የነበረው የአካባቢው የቦታ ስም አዲስ አበባ በሚል የአማራ ስም ተሰየመ። በሚቀጥሉት ዓመታትም በርካታ የፍንፍኔ ቦታዎች ስማቸው ከኦሮሚኛ ወደ አማርኛ ተለወጡ። ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል፡ ቡርቃ ፍንፍኔ "ፍልውሃ" የሚል ስም ተሰጠው፤ ብርብርሰ ያኢ ጎሮ አራዳ ጊዮርጊስ ተባለ፤ ጨፌ አራራ ስድስት ኪሎ የሚል ስም ያዘ፤ ዳለቲ ኣራት ኪሎ ተባለ፤ ቱሉ ሄጦ ዲምቱ ታላቁ ቤተመንግስት ተብሎ ተሰየመ፤ በዳ ኤጀርሳ ራስ ካሳ ሰፈር ተባለ፤ ቱሉ ኮርማ ራስ ብሩ ሰፈር በሚል ተሰየመ፤ ጎሮ ኮርማን ራስ ተሰማ ሰፈር ኣሉት፤ አርቡ ኢሬቻን ራስ ሃይሉ ሰፈር ብለው ሰየሙ ፤ሁሩፊ ቦምቢን ጃን ሜዳ ኣሉት፤ ከረ ቅርጢ የሚለውን ሰሜን በር ወደሚለው ቀየሩት፤ አዳሚን ሰሜን ማዘጋጃ ብለው ጠሩት፤ ባቦ ኣዲሱ ቄራ ተባለ፤ ቡርቃ ቆሪቻ የካ ሚካኤል በሚል ተተካ። ከዚህ በላይ የተጠቀሱት የፍንፍኔ ቦታ ስሞች ስማቸው ከተቀየሩት ጥቂቶቹ ናቸው። እነዚህ ቦታዎች ከፊሎቹ ቅዱስ የሃይማኖታዊ ስፍራዎች ነበሩ።

የአማራ ገዢዎች በኦሮሚያ ላይ ሲያካሄዱ የነበረውን ወረራ በድል እንዳጠናቀቁ  ፍንፍኔን ዋና የጦር ሰፈራቸው በማድረግ ከተሙ። በማስከተልም የመኖሪያ ሰፈራቸው ኣደረጉት። መጀመሪያ የምኒሊክ ባለቤት ጣይቱ የፍንፍኔን የተፈጥሮ ሙቅ ውሃ በመጎብኘት በአጠገቡ

የመኖሪያ ቤት ለንጉሳውያን ቤተሰብ ተሰራ። በኋላም የንጉሱ የቅርብ ዘመዶች በፍልውሃ መታጠብ ለምደው ቦታውን በመውደድ በዚያ ዙሪይ መኖሪያ ቤቶቻቸውን ሰሩ። ሌሎች የመንዝ መሳፍንትም ከነአሽከሮቻቸውና ሰራተኞቻቸው መጥተው በቦታው ሰፈሩ። አጼ ምኒሊክ ፍንፍኔን ከወታደራዊ ሰፈር(ከተማ) ወደ ዋና ከተማና የመንግስት መቀመጫ ለወጠው። በዚህ ሂደትም ትልቁን ቤተመንግስት በቱሉ ሄጦ ዲምቱ አልያም ደጋ አራራ በተባለው ስፍራ ገነባ።

የአማራ ነፍጠኞችና ሰፋሪዎች ወደ ፍንፍኔ መጉረፍን ተከትሎ በአካባቢው ሰፍሮ የነበረው የኦሮሞ ህዝብ ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ መጣ። በፍንፍኔ መሬት ላይ ይኖሩ የነበሩ ኦሮሞዎች በቅደም ተከተል የኢምፓዬሪቱን የፖለቲካ ስልጣን በያዙ መንግስታት የሃገር ባለቤትነታቸውን ተነፍገው ከቀዬያቸና ከመሬታቸው ወደ ዳር ተገፉ። ኦሮሞ ነባር ህዝብ ሆኖ እያለ በከተማው አናሳ ህዝብ ሆነ። በኢትዮጵያ አቆጣጠር በ1999(2007) በአገሪቱ የህዝብ ቆጠራ ኤጀንሲ የተካሄደው የህዝብ ቆጠራ እንደሚያመለክተው በፍንፍኔ ከተማ ውስጥ የሚኖር የኦሮሞ ህዝብ ቁጥር 19.51 በመቶ ብቻ ነበር። ከሌላ ቦታ ወደ ፍንፍኔ ፈልሰው በዚያች ከተማ የሚኖሩ የአማራ ብሄር አባላት ቁጥር ደግሞ 47.07 በመቶ መሆኑን ዘገባው ያመለክታል። በዚሁ የ1999 የህዝብ ቆጠራ የተመለከተው ሌላው ጉዳይ በከተማው ከሚነገሩ ቋንቋዎች አማርኛ 71.0 በመቶ ሲሆን የኦሮምኛ ቋንቋ ወደ 10.7 በመቶ መውረዱን ያሳያል። ይህ አሃዝ ሌላው ቀርቶ ፍንፍኔ ውስጥ ከሚኖሩ የኦሮሞ ብሄር አባላት መካከል በሚደርስባቸው የባህልና የቋንቋ ተጽእኖ ምክንያት ቋንቋቸውንና ማንነታቸውን የረሱ በርካታ ኦሮሞዎች መኖራቸውን ያመለክታል። በምሊኒክ አገዛዝ ዘመን በርካታ ኦሮሞዎች በአካል ተገፍተው ፍንፍኔን እንዲለቁ ተደረገ። በሃይለ ሥላሴ ዘመነ-መንግስት ደግሞ የኦሮሞን ባህልና ቋንቋ በማጥፋት በአማራ ቋንቋና ባህል ለመተካት ሲደረግ በነበረው ግልጽ ተጽዕኖና ፖሊሲ ኦሮሞነትን ከከተማዋ በማጽዳት የኦሮሞ ትውልዶች ቋንቋቸውንና ባህላቸውን እንዳይወራረሱ ተደረገ።

ትላልቅ ከተሞች የአንድን ህዝብ ማህበራዊ ኑሮ ማሻሻል፤ ለኢኮኖሚ፤ ለባህል፤ ለቋንቋና ለፖልትካ እድገት ትልቅ ሚና እንዳላቸው የሚታወቅ ነው። ይሁን እንጂ ፍንፍኔ ውስጥ የሚከናወኑ ማንኛውም የልማትና የባህል ስራዎች ገዢዎችን በሚጠቅሙ ፖሊሲዎችና እቅዶች ይነደፋሉ። እስካሁን የታየው ልማትና እድገት ለኦሮሞ ህዝብ የሰጠው ጥቅም የለም። የኦሮሞ ህዝብ እስከ ዛሬ በፍንፍኔ መስተዳድር ውስጥ በቀጥታ እንዳይሳተፍ መብቱን ተነፍጎ በከተማው ኢኮኖሚውን ባህሉንና ቋንቋውን እንዳያሳድግ ተደርጓል። በራሱ ጉዳይ ላይ ውሳኔ እንዳይሰጥ የፖለቲካ ስልጣን የለውም። የራሱን ልማትና የኢኮኖሚ እድገት በራሱ እቅድ እንዳይመራ መብቱን ተነፍጓል። የባዕድ ገዢዎች ኦሮሞ የከተማ ነዋሪ እንዳይሆን ሆነ ብለው የከተማ አስተዳድር መዋቅሮችንና ፖሊሲዎችን እነርሱን በሚጠቅም መልክ ይዘረጋሉ። የኦሮሞን ህዝብ የሚጎዱ ፖሊሲዎችን በህዝቡ ላይ በሃይል ይጭናሉ። ይህ ማለት የኦሮሞ ህዝብ በፍንፍኔ ላይ የማዘዝ መብት መነፈጉ የልማት ተቋማትና ባህሉን ፍንፍኔ ውስጥ እንዳያስፋፋ እንቅፋት ሆኗል። የኦሮሞ ከፍንፍኔ መገለል ባጠቃላይ በኦሮሚያና በኦሮሞ ህዝብ ላይ እያደረሰ ያለው ተጽዕኖ ወደር የለውም።

ከዚህ በላይ ከፍ ብለን መጥቀስ እንደሞከርነው ስልጣን ላይ ያለው የወያኔ-ኢህአዴግ መንግስት ኦሮሞን በሚመለከት እያራመደ ያለው ፖሊሲ ቀደም ሲል የነበሩ ስርዓቶች ሲያራምዱ ከነበሩት ጋር ተመሳሳይነት አለው። ልዩነት ያለው የአማራን የበላይነት በትግራይ የበላይነት መተካት ብቻ ነው። የወያኔ ኢህአዴግ መንግስት ከቀድሞ ገዢዎች የወረሰውን ኦሮሞን ከመሬቱ የማፈናቀል ፖሊሲ በሌላ መልክ ቀጥሎበታል።

የወያኔ መሪዎች እኩይ ኣላማቸውን ለማሳካት ኦሮሚያንና የኦሮሞ ህዝብ ብዛት በመቀነስ ኣናሳ ህዝብ ለማድረግ ላለፉት 23 ዓመታት ያለማቋረጥ እየሰሩ ይገኛሉ። ላለፉት 23 ዓመታት በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ኦሮሞዎችን ከኣያት ቅድመ-ኣያቶቻቸው መሬት ኣፈናቅሏል። በዝርፊያና ቅሚያ የሚታወቀው የወያኔ ስርዓት በ1983(1991) ስልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ የኦሮሚያን ኢኮኖሚና የተፈጥሮ ሃብት ከከተማ እስከ ገጠር ያለውን ተቆጣጥሮታል። እንደ እርሻ መሬት፡ የግጦሽ መሬት፡ ወንዞች፡ ደኖች፡ ማዕድናት፡ ሃይቆችና የማዕድን ውሃዎች ሳይቀሩ በሃይል ተቆጣጥረው እየተጠቀሙበት ነው። ጠቅላላ የኦሮሚያ የተፈጥሮ ሃብቶችን የንግድ ሸቀጥ በማድረግ እየቸበቸቡ ይገኛሉ። በዛሬ ዘመን የኦሮሞ መሬትና ህዝቡ የወያኔ የግል ንብረቶች ናቸው ማለት ይቻላል። የወያኔ መሪዎች የኦሮሞን መሬት መጠቀም ብቻ ሳይሆን ህዝቡን ከመሬቱ እያፈናቀሉ ለውጪ ባለሃብቶች ዳጎስ ባለ የውጪ ምንዛሪ ይሸጡታል። በኦሮሚያ ከኣርሶ ኣደር መሬት ቀምቶ ለውጪ ባለሃብቶች መሸጥ የተለመደ ሆኗል። ወያኔዎች በሚሊዮኖች ሄክታር የሚገመት መሬት ከኦሮሞ ኣርሶ ኣደሮች ቀምቶ ለህንድ፡ ቻይና፡ ማለዢያ፡ ፓኪስታንና ለዐረብ ኩባንያዎች በከፍተኛ ገንዘብ ሸጠዋል። በተመሳሳይ ለሌሎች የአገር ውስጥና ኣለማቀፍ ኢንቨስተሮች በመሸጥ ላይ ይገኛል። ከዚህም በተጨማሪ የራሱ ትላልቅ የንግድ ኩባኒያዎችንና ኢንዱስትሪዎች በኦሮሚያ በተለይ ደግሞ በፍንፍኔ እንደ እንጉዳይ ፈልተው ግልጽ ዘርፊያ እያካሄዱ ናቸው። ወያኔዎች እርጉም የሆነውን እስትራቴጂያቸውን እውን ለማድረግ ከፍንፍኔና ኣካባቢው ኦሮሞዎችን በመጠራረግ በመበተን ላይ ይገኛሉ።

በ1987(1995) ለይስሙላ ቢሆን ራሱ በወያኔ-ኢህአዴግ  የተጻፈው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሪፑብሊክ ህገ-መንግስት በአገሪቷ ውስጥ የሚገኙ ብሄር-ብሄረሰቦች የራሳቸውን እድል በራሳቸው የመወሰን መብት፡ በራሳቸው ጉዳይ ውሳኔ የመስጠት፡ በራሳቸው የተፈጥሮ ሃብትና የልማት እቅዶች ላይ የማዘዝ መብት ባህላቸውን ቋንቋቸውንና ታሪካቸውን የማበልጸግ መብቶችና የመሳሰሉት እንዳላቸው ይደነግጋል። የአዲስ ኣበባን ከተማ አስመልክቶ በህገ-መንግስቱ ኣንቀጽ 49 ቁጥር-5 ላይ የሰፈረው ደግሞ እንዲህ ይላል፡ “በፍንፍኔ ውስጥ የኦሮሚያ ልዩ ጥቅም፡ የማህበራዊ ኣገልግሎቶች ወይም የተፈጥሮ ሃብትን ኣጠቃቀምና የመሳሰሉት እንደዚሁም ፍንፍኔ በኦሮሚያ ውስጥ ከመገኘቷ ጋር በተያያዘ ስለጋራ ኣስተዳደር ሊነሱ የሚችሉ ሁሉ ይከበራሉ። ለዝርዝሮቹም ህግ ይወጣል።” ይሁን እንጂ ይህንን ጉዳይ በሚመለከት ይወጣል ተብሎ በህገ-መንግስቱ የሰፈረው መብት እስከኣሁን ኣልወጣም። እነሆ ህገ-መንግስቱ ከተጻፈ 19 ዓመታትን ኣስቆጥሯል። በመሆኑም ኦሮሚያ እስካሁን ከፍንፍኔ ከተማ የተጠቀመችው ምንም ነገር የለም። ይልቁንስ በተቃራኒው የፌዴራሉ መንግስት ፍንፍኔን ማስፋፋትና ማሳደግ በሚል ከኦሮሚያ እየተጠቀመ ይገኛል። በወያኔ ህገ-መንግስት መሰረት ፍንፍኔ የፌዴራል መንግስት መቀመጫና ዋና ከተማ ከመሆን ኣልፋ እንደ ኣንድ የክልል መንግስት የተዋቀረች መንስግት ናት። በሌላ በኩል ለይስሙላ የኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት መቀመጫና ዋና ከተማ እንደሆነች ይነገራል።  የሆነ ሆኖ ፍንፍኔ የፌዴራሉ መንግስት ኣካል እንደመሆኗ መጠን የፌዴራሉ ፓርላማ በፍንፍኔ ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ህግ ሊያወጣ ይችላል። የፌዴራሉ መንግስት ባሻው ጊዜ በህዝብ የተመረጠውን የፍንፍኔ ምክር ቤት ኣፍርሶ ራሱ የፈለገ ሹማምንት ይሾማል። ይህ በተግባር የታየ ጉዳይ ነው።

እዚህ ላይ ኣበክረን መግለጽ የምንፈልገው ከመጀመሪያው ፍንፍኔ እንደ ኣንድ ክልላዊ መንግስት እንድትዋቀር የተደረገበት ምክንያት ከእናቷ ከኦሮሚያ ለመለየት ሆን ተብሎ የተደረገ ነው። ፍንፍኔ በጂኦግራፊያዊ ኣቀማመጧ ወሳኝ ቦታ ላይ የምትገኝ የኦሮሚያ ኣካል መሆኗ የሚያጠያይቅ ጉዳይ ኣይደለም። በታሪክም በህግም የኦሮሞዎች መሬት ናት።

ይህ ሆኖ ሳለ ወያኔ ኢህአዴግ ሆን ብሎ ፍንፍኔን በኣስተዳደር፡ በኢኮኖሚና ማህበራዊ አገልግሎቶች ከኦሮሚያ ነጥሎ ለብቻ አዋቀራት። ይባስ ብሎ በሺዎች የሚቆጠሩ የኦሮሞ ሰራተኞችና አርሶ አደሮችን ከፍንፍኔና አካባቢዋ አፈናቀለ። እንደዚሁም የኦሮሞ እርዳታ ድርጅትና የመጫ- ቱለማ መረዳጃ ማህበርን ጨምሮ በርካታ የኦሮሞ ተቋማትን ከፍንፍኔ አስወገዳቸው። ሌላው ቀርቶ ስርዓቱን የሚያገለግሉ የኦሮሚያ አስተዳደር ቢሮዎችንና ተቋማት በ1994(2002)ዓም ፍንፍኔን ለቀው እንዲወጡ በወያኔ መንግስት ትዕዛዝ መተላለፉ የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው። እውነቱን ለመናገር ኣሁን ያለው የኦሮሚያ መንግስት ቋሚ መቀመጫ የለውም። ኦሮሚያም ቋሚ ዋና ከተማ የላትም። የወያኔ መንግስት ላለፉት 23 ዓመታት ሆን ብሎ የኦሮሚያን መሬት ቆራርሶ ወደ ትግራይና ሌሎች ብሄር ብሄረሰቦች ሲያካልል መሰንበቱም አይዘነጋም።

ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው ወያኔ ፍንፍኔን ከኦሮሚያ ገንጥሎ እንደ አንድ መስተዳድር ማዋቀሩ እንደዚሁም የፍንፍኔ አጎራባች ከተሞችን ፍንፍኔ ስር ለማስገባት የሚደረገው ጥረት ዓላማው የኦሮሚያን ድንበር ሸራርፌው ለማሳነስና ቢቻል ደግሞ እንደ ክልላዊ መስተዳደር ልትቀጥል የማትችልበትን አስቸጋሪ ሁኔታ ለመፍጠር የሚሸረብ ደባ ነው። ዓላማው ከኦሮሚያ መሬቶችን ቦጫጭቀው ወደ ፍንፍኔ በመቀላቀል በኦሮሚያ እምብርት ላይ ሌላ ትልቅ ሃገር በመፍጠር በቀሪዎቹ የኦሮሚያ ዞኖች መካከል አጥር ለመገንባት የታሰበ ሸፍጥ ነው። ከዚህ በስተጀርባ ያለው የፖለቲካ ዓላማ ግልጽ ነው። ይኸውም በመሃል ኦሮሚያ ጋሬጣ በመትከል የኦሮሞ ህዝብ የራስን እድል በራስ የመወሰን ጥያቄን ለማወሳሰብና ግቡን እንዳይደርስ ለማደናቀፍ ነው። ፍንፍኔ የፌዴራል መንግስቱ መቀመጫ፡ የአገሪቱ ዋና ከተማ፡ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማዕከል እንደዚሁም የቀጠናና የአለማቀፍ ድርጅቶች መቀመጫና የዲፕሎማሲ ማዕከል መሆኗ ግልጽ ነው። የአፍሪካ ህብረት፤ በተባበሩት መንግስታት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን የመሳሰሉት ተቋማት በአዲስ አበባ ይገኛሉ። የአፍሪካ ህብረት በቅርቡ በወያኔ መንግስት በተቸረለት ሰፊ የኦሮሞ መሬት ላይ የቢሮ ህንጻዎችንና አዳራሾችን ሰርቶ መደላደሉ ይታወሳል። የወያኔ መንግስት ዓለማቀፍ ማህበረሰብና የውጪ ሃገር ኢንቨስተሮችን ወደ ኦሮሚያ በተለይ ወደ አዲስ አበባ ለመሳብ የሚያደርገው ጥረት የኦሮሞ ህዝብ የራስ እድል በራስ መወሰን ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር ነው።

ከዚህም ባሻገር የወያኔ መንግስትና ኣጋፋሪዎቹ የጋራ ልማትና ኢኮኖሚ እንደዚሁም ከተሞችን ማሳገድ በሚል ሰበብ ኦሮሚያ እንደ ክልላዊ መንግስት እንዳትቀጥል ለማድረግ ሌተቀን እየሰሩ ነው። የኦሮሞ ህዝብ ኣያሌ መስዋዕት ከፍሎ የተጎናጸፋቸው ኣንዳንድ የማይናቁ ድሎችን ለመፋቅ ተግተው በመስራት ላይ ይገኛሉ። ይሁን እንጂ እንደዚህ ኣይነቱ ኣካሄድ ወደ ባሰ የደም መፋሰስ እያመራ መሆኑ በግልጽ እየታየ ነው።

በወያኔ ኢህአድግ አዲስ የተወጠነው የፍንፍኔ (አዲስ አበባ) ማስተር ፕላን ወይም ካርታ ኣሁንም ተቃውሞ ቀስቅሶ በመላው ኦሮሚያ የኦሮሞ ተማሪዎችና ህዝቡ ተቃውሞ በማሰማት ላይ ናቸው። ማስተር ፕላኑ ትልቅ ውግዘት ገጥሞታል። የኦሮም ተማሪዎችንና ህዝቡ ጭቆና አንገሸገሸን፡ በቃን ብለው መሰረታዊ ጥያቄዎችን አንግበው ከስርዓቱ ታጣቂዎች ጋር ትንቅንቅ ይዘዋል። የወያኔ መንግስት በሰላማዊ መንገድ የቀረበውን ጥያቄ ከመጠን ያለፈ ሃይል ተጠቅሞ በጦር መሳሪያ ለማፈን እየጣረ ይገኛል። ኣግኣዚ የተባለው ታማኝ የወያኔ ጦር በሰላማዊ መንገድ ሰልፍ የወጡ የኦሮሞ ተማሪዎችና ህዝብ ላይ ተኩሶ በጠራራ ጸሃይ እየገደላቸው ነው። እስከ ኣሁን በኣስርታት የሚቆጠሩ የኦሮሞ ዜጎች ከወያኔ ሰራዊት በተተኮሰባቸው ጥይት ሞተዋል። በርካቶች ቆስለዋል። በመቶዎች የሚቆጠሩ ታፍነው ወዳልታወቁ እስር ቤቶች ተወስደዋል። የወያኔ ልዩ ጦር የሆነው ኣግኣዚ በኣምቦ፡

ጉደር፡ በቶኬ፡ በባሌ-ሮቤ፡ ግምቢ፡ በሃረማያ፡ በቄለምና የሌሎች የኦሮሚያ ኣካባቢዎች ሰላማዊ ሰልፍ በወጡ የኦሮሞ ዜጎች ላይ ኣነጣጥሮ በመተኮስ በደማቸው ዋኘርቷል። ይህ የወያኔ ኣረመኔያዊ እርምጃ ስርዓቱ ፖሊሲዎቹን በመሳሪያ ሃይል ተግባራዊ ለማድረግ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ያመለክታል።

በሌላ በኩል የወያኔ ስርዓት መሬት ላይ ያለውን እውነታ ለማድበስበስ ኣደንቋሪ ፕሮፓጋንዳውን በመገናኛ ብዙሃን እየነዛ ነው። በየቦታው ህዝብን ኣስገድዶ ስብሰባ በማድረግ የፍንፍኔን ማስተር ፕላን አስመልክቶ የተዛባ መረጃ በመስጠት ላይ ይገኛል። ይህን ጉዳይ ኣስመልክተው የወያኔ ባለስልጣናትና ተለጣፊው የኦህዴድ መሪዎች የሚሰጡት መግለጫዎች የሚጋጩና የማይጣጣሙ ናቸው። ግልጽነት እጅግ ይጎድለዋል። በመሬትና በካርታ ላይ ያለው እውነታ ሌላ ሆኖ እያለ የሌለ ነገር ሊነግሩን ይሞክራሉ። ካርታ ላይ ያለው ሀቅ ፍንፍኔን ኣሁን ሸፍና ካለችው 54,000 ስኴር ኪሎ ሜትር ወደ 1.2 ሚሊዮን ስኴር ኪሜ ለመዘርጋት ነው። ይህ ሆኖ ሳለ በተላላኪዎቻቸው ኣማካይነት ህዝቡን ለመሸንገል "ማስተር ፕላኑ የፊንፊኔን ከተማ ወደ ኦሮሚያ ክልል ማስፋፋትና ኣጎራባች ከተሞችን በዋና ከተማው መስተዳድር ስር ለማስገባት ኣይደለም" ብለው ኣይናቸውን ጨፍነው ይክዳሉ። ይህ ጉዳይ አዲስ አበባን ለማስፋፋት የታቀደ ኣይደለም የሚሉ ከሆነ የአዲስ አበባ ከተማ ማስተር ፕላን በሚል ስም የከተማዋን አዲስ ካርታ መስራት ለምን ኣስፈለገ ተብለው ቢጠየቁ ግን መልስ የላቸውም። ስለዚህ የተያያዙት የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ህዝቡን በመሸንገል አቅጣጫ ለማስቀየርና እንቅስቃሴያቸውን ለማብረድ የታለመ መሆኑ ግልጽ ነው። እንዲህ ኣይነቱ ኣሰልቺ ፕሮፓጋንዳ አዲስ ኣይደለም። ወያኔ ላለፉት 23 ዓመታት ይህንኑ ሲለማመድ ነው የኖረው። በፕሮፓጋንዳና በቅጥፈት ሃገርን ለመምራት የሚሞክር መንግሥት ነው። እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት ጉዳይ ቢኖር የኦሮሞ ህዝብ ተቃውሞ የፍንፍኔ ከተማ ወደ ኦሮሚያ መስፋፋትን ብቻ ኣይደለም። በርካታ ያልተመለሱ መሰረታዊ ጥያቄዎች ኣሉት። መሰረታዊው የኦሮሞ ህዝብ የራስን ዕድል በራስ መወሰን ጥያቄ ገና አልተመለሰም።

አሁን ያለው ተጨባጭ ሁኔታ ለኦሮሞ ህዝብ ፈታኝ ጊዜ ነው። የኦሮሞ ህዝብ በጠላቶቹ ወደ ጠንካራ ኣለት እየተነዳ ነው። ስለዚህ ህዝቡ ኦሮሚያንና የኦሮሞን ማንነት ለማጥፋት ቆርጦ የተነሳውን ጠላት ከመመከት ውጪ የቀረው ሌላ ኣማራጭ የለውም። ይህ ደግሞ ሆይ ብለው በኣንድነት መነሳትን ይጠይቃል። የኦሮሞ ህዝብ ከመሬቱ እያፈናቀለ፡ የኦሮሞን ሃብት በመዝረፍ ህዝቡን እንደ ኣውሬ ኣድኖ የሚጨፈጭፈውን ጠላት በኣንድነት ተነስቶ መከላከል ይኖርበታል።

የኦሮሞ ነጻነት ግንባር፡ ፍንፍኔ የኦሮሚያ እንምብርትና ወሳኝ ኣካል ናት ብሎ ያምናል። በዚህ መሰረት የፍንፍኔ እጣ ፈንታ ከኦሮሚያ እጣ ፈንታ ተለያይቶ የሚታይ ጉዳይ ኣይደለም። ፍንፍኔን ነጻ ለማውጣት የሚደረገው ትግል ለኦሮሚያ ነጻነት የሚደረግ ትግል ኣካል ነው። ባጠቃላይ የፍንፍኔና የኦሮሚያ ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ወገኖች በሙሉ በኣንድነት ተነስተው ራሳቸውንም ሆነ ኦሮሚያን ከጥፋት መታደግ ኣለባቸው። የኦሮሞ ወጣቶች፡ ተማሪዎች፡ ሰራተኞች፡ ኣርሶ ኣደሮችና ሌሎች የህብረተሰቡ ክፍሎች ሁሉ እጅ ለእጅ ተያይዘው ለኦሮሚያ ነጻነትና ለኦሮሞ ህዝብ መብት መታገል ይኖርባቸዋል።

**ድል ለኦሮሞ ህዝብ!**

**የኦሮሞ ነጻነት ግንባር**

**ግንቦት፡ 2014**